2023-2024

# የቅድመ-ሙአለህፃናት/ሄድስታርት
# የቀን መቁጠርያ (ካላንደር)









የልጅ ስም፡- ______________________________

ለቅድመ ሙዓለ ህፃናት/ሄድ ስታርት ክፍል የቤተሰብ

አገልግሎት ሠራተኛ ተመድቧል። ______________________

ስልክ፡- 240-740-4530

Maryland's Largest School District

MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

# 2023–2024 ቅድመ ሙዓለህፃናት/ሄድ ስታርት ካለንደር

| 2023 | |
|---|---|
| ኦገስት 21—25 | የመምህራን ፕሮፌሽናል ቀን |
| ኦገስት 28 | የተማሪዎች የት/ቤት መጀመሪያ ቀን ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል (K-12) |
| ኦገስት 28 እስከ ሴፕቴምበር 1 | ሄድስታርት የቤት/የቤተሰብ ጉብኝት—ቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሄድ ስታርት ተማሪዎች ት/ቤት አይኖርም |
| ሴፕቴምበር 4 | የሰራተኞች ቀን (ሌበር ዴይ) — ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ናቸው። |
| ሴፕቴምበር 5 እና 6 | ለሄድ ስታርት እና ቅድመ መዋእለ ህጻናት ጀማሪ ተማሪዎች በፈረቃ ይከፈታል |
| ሴፕቴምበር 7 | ለሁሉም ሄድ ስታርት/ቅድመ-መዋእለ ህጻናት ተማሪዎች የመጀመሪያ ቀን |
| ስፕቴምበር 22 | ሁሉም ተማሪዎች ቀደም ብለው የሚለቀቁበት ቀን |
| ስፕተምበር 25 | ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት አይኖርም። |
| ኦክተበር 5 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ – 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ / ዙም (Zoom) |
| ኦክቶበር 6 | የሄድ ስታርት ለወላጆች የሚሰጡ መግለጫዎች ይጠናቀቃሉ |
| ኦክቶበር 9 | ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት የለም። |
| ኦክተበር 18 | የቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሄድ ስታርት መምህራን ስልጠና — ለቅድመ መዋዕለ ሕፃናት እና ለሄድ ስታርት ተማሪዎች (Group A) ትምህርት የለም |
| ኦክቶበር 19 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ - 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ኦክቶበር 25 | የቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሄድ ስታርት መምህራን ስልጠና—ለቅድመ መዋዕለ ሕፃናት እና ለሄድ ስታርት ተማሪዎች (Group B) ትምህርት የለም |
| ኦክተበር 31 | የቅድመ ሙዓለህፃናት መግለጫ ይጠናቀቃል |
| ኖቨምበር 1 | ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት አይኖርም፥ የሩብ አመት እቅድ መጨረሻ |
| ኖቨምበር 2 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ – 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ / ዙም (Zoom) |
| ኖቬምበር 9 | የአባትነት ተግባር – 6:30 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ኖቨምበር 16 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ - 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ኖቨምበር 20 እና 21 | የወላጅ-መምህር ኮንፈረንስ—ለቅድመ መዋዕለ ህጻናት እና ለሄድ ስታርት ተማሪዎች ትምህርት ቤት የለም። |
| ኖቨምበር 22፥ 23 እና 24 | ታንክስጊቪንግ (Thanksgiving)— ት/ቤቶች እና ጽ/ቤቶች ዝግ ናቸው |
| ዲሴምበር 4-7 | ብሔራዊ የሄድ ስታርት የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ኮንፈረንስ፣ New Orleans, LA |
| ዲሰምበር 6 | የቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሄድ ስታርት መምህራን ስልጠና—ለቅድመ መዋዕለ ሕፃናት እና ለሄድ ስታርት ተማሪዎች (Group A) ትምህርት የለም |
| ዲሰምበር 7 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ – 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ / ዙም (Zoom) |
| ዲሴምበር 13 | የቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሄድ ስታርት መምህራን ስልጠና—ለቅድመ መዋዕለ ሕፃናት እና ለሄድ ስታርት ተማሪዎች (Group B) ትምህርት የለም |
| ዲሴምበር 15 | ዊንተር ላይትስ (ብርሃን) ክውነት |
| ዲሰምበር 21 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ - 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ዲሴምበር 25-29 | የዊንተር ዕረፍት—ለተማሪዎች እና ለአስተማሪዎች ትምህርት ቤት የለም፤ ቢሮዎች ዲሴምበር 25 እና ጃንዋሪ 1 ዝግ ይሆናሉ |

| 2024 | |
|---|---|
| ጃንዋሪ 1 | ዊንተር እረፍት— ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ናቸው |
| ጃኑዋሪ 2 | ዊንተር እረፍት—ለተማሪዎች እና ለመምህራን ት/ቤት አይኖርም |
| ጃንዋሪ 3 | ክፍል ይጀመራል |
| ጃኑዋሪ 4 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ – 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ / ዙም (Zoom) |
| ጃንዋሪ 11 | የአባትነት ተግባር – 6:30 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ጃንዋሪ 15 | የዶ/ር ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁንየር (Dr. Martin L. King፣ Jr.) ቀን—ት/ቤቶች እና ጽ/ቤቶች ዝግ ናቸው |
| ጃንዋሪ 18 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ - 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ጃኑዋሪ 29 | ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት አይኖርም፥ የሩብ አመት እቅድ መጨረሻ |
| ጃኑዋሪ 30 እስከ ፌብሩዋሪ 2 | ሔድ ስታርት ቤት/ቤተሰብ ጉብኝት— ለሄድ ስታርት ተማሪዎች ት/ቤት አይኖርም |
| ፌብሩወሪ 1 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ – 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ / ዙም (Zoom) |
| ፌብሯሪ 7 | የቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሄድ ስታርት መምህራን ስልጠና—ለቅድመ መዋዕለ ሕፃናት እና ለሄድ ስታርት ተማሪዎች (Group A) ትምህርት የለም |
| ፌብሩዋሪ 15 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ - 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ፌብርዋሪ 19 | የፕሬዚደንት ቀን— ት/ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ናቸው |
| ፌብሩዋሪ 22 | የቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሄድ ስታርት መምህራን ስልጠና—ለቅድመ መዋዕለ ሕፃናት እና ለሄድ ስታርት ተማሪዎች (Group B) ትምህርት የለም |
| ማርች 1 | ሁሉም ተማሪዎች ቀደም ብለው የሚለቀቁበት ቀን |
| ማርች 7 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ – 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ / ዙም (Zoom) |
| ማርች 14 | የአባትነት ተግባር – 6:30 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ማርች 21 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ - 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ማርች 25 እስከ ኤፕሪል 1 | የስፕሪንግ እረፍት—ለተማሪዎች እና ለመምህራን ት/ቤት አይኖርም፣ ቢሮዎች ዝግ ናቸው ማርች 27—ኤፕሪል 1 |
| ኤፕሪል 4 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ – 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ / ዙም (Zoom) |
| ኤፕሪል 10 | ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት የለም። |
| ኤፕሪል 15-18 | ብሔራዊ ሄድ ስታርት ኮንፈረንስ – Portland, OR |
| ኤፕሪል 18 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ኤፕሪል 22 | ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት የለም። |
| ሜይ 2 | የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ – 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ / ዙም (Zoom) |
| ሜይ 14 | የፕራይመሪ ምርጫ ቀን - ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ናቸው። |
| ሜይ 16 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ - 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ሜይ 27 | ሜሞሪያል ዴይ (Memorial Day)— ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ናቸው |
| ጁን 6 | የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ - 6:00 PM – ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) |
| ጁን 12 | ለሁሉም ቅድመ-ሙአለህፃናት/ሄድ ስታርት ተማሪዎች የመጨረሻ የትምህርት ቀን |
| ጁን 13 | ትምህርት ቤት የመጨረሻ ቀን ከመዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል (K-12) |
| ጁን 14 | ለመምህራን የሙያ ቀን |
| ጁን 19 | ጁንቴንዝ/Juneteenth - ት/ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ናቸው |



# ኦገስት 2023

| ጁላይ 2023 | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| S/እ | M/ሰ | T/ማ | W/ሮ | T/ሐ | F/ዓ | S/ቅ |
| | | | | | | 1 |
| 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
| 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 |
| 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 |
| 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 |
| 30 | 31 | | | | | |

| ሴፕቴምበር 2023 | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| S/እ | M/ሰ | T/ማ | W/ሮ | T/ሐ | F/ዓ | S/ቅ |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 |
| 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 |
| 29 | 30 | 31 | | | | |

| እሁድ | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 |
| 20 | 21<br>የመምህራን የሙያ/ፕሮፌሽናል ቀን<br>[መደበኛ ካለንደር ለሚጠቀሙ ት/ቤቶች ብቻ/TRADITIONAL CALENDAR SCHOOLS ONLY] | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 |
| 27 | 28<br>ለተማሪዎች የመጀመሪያ የትምህርት ቀን (K–12)<br>ሔድ ስታርት ቤት/ቤተሰብ ጉብኝት— ለቅድመ መዋእለ ህጻናት (Pre-K) እና ሔድ ስታርት ተማሪዎች ት/ቤት አይኖርም | 29<br>ሔድ ስታርት ቤት/ቤተሰብ ጉብኝት— ለቅድመ መዋእለ ህጻናት (Pre-K) እና ሔድ ስታርት ተማሪዎች ት/ቤት አይኖርም | 30<br>ሔድ ስታርት ቤት/ቤተሰብ ጉብኝት— ለቅድመ መዋእለ ህጻናት (Pre-K) እና ሔድ ስታርት ተማሪዎች ት/ቤት አይኖርም | 31<br>ሔድ ስታርት ቤት/ቤተሰብ ጉብኝት— ለቅድመ መዋእለ ህጻናት (Pre-K) እና ሔድ ስታርት ተማሪዎች ት/ቤት አይኖርም | | |

**ጥሩ መፅሃፎችን ማንበብና መጋራት/የካውንቲውን አውደ ርእይ መጎብኘት።**

# ቅድመ-ሙዓለህፃናት/ሄድ ስታርት ሠራተኞች

**አስተዳደር . . . . . . . . . . 240-740-4530**

Jessica Blasic . . . . . . . . . . ሱፐርቫይዘር፣
(Pre-K/HS) ቅድመ-መዋእለ ህጻናት እስከ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት
Michelle Esema . . . . . . . . . . አስተባባሪ
Valerie Ashton . . . . . . . . . . የሄድ ስታርት ፕሮግራም ማኔጀር
Gloria Diaz . . . . . . . . . . አካውንታንት
Kevin Shim . . . . . . . . . . የዳታ ሲስተም ኦፕሬተር
Elsa Rios . . . . . . . . . . ዳታ ሲስተም ኦፕሪተር
Jocelyn Joya . . . . . . . . . . የአስተዳደር ጸሐፊ
Jeannette Zepeda Escobar . . . . . . . . . . የስተዳደር ጸሐፊ
Joanna Vasquez . . . . . . . . . . ሬጅስትራር
Flor Martinez . . . . . . . . . . ሬጅስትራር

**የጨቅላ ልጆች እድገት እና የጤና አገልግሎቶች—
የትምህርት ሠራተኞች**
EDUCATION STAFF . . . . . . . . . . 240-740-4530

Rhonda Amissah . . . . . . . . . . የትምህርት ስፔሻሊስት
Kelly Barrett . . . . . . . . . . የትምህርት ስፔሻሊስት
Stephanie Brink . . . . . . . . . . የትምህርት ስፔሻሊስት
Deirdra Fuller . . . . . . . . . . የትምህርት ስፔሻሊስት
Jiji Olds . . . . . . . . . . የትምህርት ስፔሻሊስት
Louise Tolin . . . . . . . . . . የትምህርት ስፔሻሊስት
Shalini Komal . . . . ዋና ጽ/ቤት የቅድመ መዋእለ ህጻናት አስተማሪ
Shona Weaver . . . . ዋና ጽ/ቤት የቅድመ መዋእለ ህጻናት አስተማሪ
Susan Dowling . . . . . . . . . . የፕሮግራም ድጋፍ መምህርት
Sonali Motha . . . . . . . . . . የፕሮግራም ድጋፍ መምህርት
Maree Nicoll . . . . . . . . . . የፕሮግራም ድጋፍ መምህር/ት
Gabriella Estevez . . . . . . . . . . ሳይኮሎጂስት
Sara McKeen . . . . . . . . . . ሳይኮሎጂስት
Marissa Senese . . . . . . . . . . ሳይኮሎጂስት
Julie Shields . . . . . . . . . . ሳይኮሎጂስት
Victoria Willingham . . . . . . . . . . ሳይኮሎጂስት
Joe Ann Robinson . . . . . . . . . . የንግግር/ቋንቋ ባለሙያ
Lynne Teoman . . . . . . . . . . የንግግር/ቋንቋ ባለሙያ

**ሞንትጎመሪ ካውንቲ** MONTGOMERY COUNTY
**የጤና ጥበቃ እና** DEPARTMENT OF HEALTH AND
**የሰብአዊ አገልግሎት መምሪያ** HUMAN SERVICES
(DHHS) . . . . . . . . . . 240-777-1553

Beka Urgessa . . . . . . . . . . የጤና አገልግሎት ኃላፊ
Lesley Konigsburg . . . . . . . . . . የጥርስ ሃይጅን ባለሙያ
Teresa Soodak . . . . . . . . . . የጥርስ ሃይጅን ባለሙያ
Wond Workalemahu . . . . . . . . . . የብቃት ማረጋገጫ ስፔሻሊስት
Norma Davis . . . . . . . . . . የጤና ረዳት
Terri Hock . . . . . . . . . . የጤና ረዳት
Cheryl Pyle . . . . . . . . . . የጤና ረዳት
Mina Aliabadi . . . . . . . . . . ነርስ
Pamela Gambon . . . . . . . . . . ነርስ
Renee McNevin . . . . . . . . . . ነርስ
Kimberly Muhammed . . . . . . . . . . ነርስ
Nomvuyo Qubeka . . . . . . . . . . ነርስ
Simone Roberts . . . . . . . . . . ነርስ
Patricia Winters . . . . . . . . . . ነርስ
Nina Munck . . . . . . . . . . ነርስ

# ወላጅ፣ ቤተሰብ፣ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ

**የማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኞች**
SOCIAL SERVICES STAFF . . . . . . . . . . 240-740-4530

Lisa Conlon . . . . . . . . . . የማህበራዊ አገልግሎት ስፔሻሊስት
Terry Fisher Thompson . . . . . . . . . . የማህበራዊ አገልግሎት ሠራተኛ
Renee Foster . . . . . . . . . . የማህበራዊ አገልግሎት ሠራተኛ
Annette Harris . . . . . . . . . . የማህበራዊ አገልግሎት ሠራተኛ
Traci Powell . . . . . . . . . . የማህበራዊ አገልግሎት ሠራተኛ
Jose Roberto Flores . . . . . የወላጅ ተስትፎ/የበጎፈቃድ ስፔሻሊስት
Maral Abkarian . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Kiara Austin . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Jazmina Begazo . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Elsi Bonilla . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Cachet Carter . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Jocelyn Chica Valdez . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Lestine Colbert . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Sandra Cruz . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Teresa Delgadillo . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Damara Dockery . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Michelle Dove . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Reyna Escamilla . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Esperanza Flores . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Deborah Garcia . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Sonia Granados . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Vianka Hardy . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Terri Harris . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Vicki Johnson . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Nuha Khalaf . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Patty Marroquin . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Leida Martinez . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Ruth Meininger . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Sorangel Peralta . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Myrna Perez . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Tania Quintanilla . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Amabilia Reyes . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Daniela Rodriguez . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Traci Stevens . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Renee Teneyck . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Rosy Turcios . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ
Cesiah Ventura . . . . . . . . . . የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ



# ሴፕቴምበር 2023

| ኦገስት 2023 | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| S/እ | M/ሰ | T/ማ | W/ሮ | T/ሐ | F/ዓ | S/ቅ |
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 |
| 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 |
| 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 |
| 27 | 28 | 29 | 30 | 31 | | |

| ኦክቶበር 2023 | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| S/እ | M/ሰ | T/ማ | W/ሮ | T/ሐ | F/ዓ | S/ቅ |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 |
| 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 |
| 29 | 30 | 31 | | | | |

| እሁድ | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | **1**<br>ሔድ ስታርት ቤት/ቤተሰብ ጉብኝት—<br>ለቅድመ መዋእለ ህጻናት እና ሔድ ስታርት ተማሪዎች ት/ቤት አይኖርም | **2** |
| **3** | **4**<br>ሌበር ዴይ/LABOR DAY—<br>ት/ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ናቸው | **5**<br>ለሔድ ስታርት እና ለቅድመ መዋእለ ህጻናት ተማሪዎች በቅደም ተከተል ይከፈታል | **6**<br>ለሔድ ስታርት እና ለቅድመ መዋእለ ህጻናት ተማሪዎች በቅደም ተከተል ይከፈታል | **7**<br>ሔድ ስታርት እና ቅድመ መዋእለ ህጻናት ተማሪዎች የመጀመሪያ ቀን | **8** | **9** |
| **10** | **11** | **12** | **13** | **14** | **15** | **16** |
| **17** | **18** | **19** | **20** | **21** | **22**<br>ሁሉም ተማሪዎች ቀደም ብለው የሚለቀቁበት ቀን | **23** |
| **24** | **25**<br>ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት አይኖርም። | **26** | **27** | **28** | **29** | **30** |

**ስለት/ቤት የወደድከ(ሽ)ውን ስእል ስራ/ሪ**

## የወላጅና መምህር ህብረት (PTA) ስብሰባዎች

- የኤሌሜንታሪ ት/ቤቶች—በየወሩ የመጀመርያው ማክሰኞ ምሽት የስብሰባ ሠዓትና ቦታ ለማወቅ የአካባቢዎን ት/ቤት ድረ-ገጽ ይጎብኙ ወይም ወደ ት/ቤቱ ጽ/ቤት ይደውሉ።
- የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች—በየወሩ ሁለተኛው ማክሰኞ ምሽት

### የትምህርት ቦርድ ስብሰባዎች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ በዚህ ወቅት በየወሩ ሁለት የሥራ ስብሰባዎችን ያካሄዳል። በተለምዶ 2:00 p.m ላይ የሚጀመረው የሥራ ስብሰባ እና 5:30 p.m. የሚጀመረው የምሽት ስብሰባ፦ ስብሰባዎቹ የሚካሄዱበት አድራሻ፦ Carver Educational Services Center, 850 Hungerford Drive, Rockville, MD 20850 ስለመጪዎቹ የቦርድ ስብሰባዎች ማናቸውም ጥያቄ ካለዎት የቦርድ ጽ/ቤትን በስልክ ቁጥር 240-740-3030 ወይም በኢ-ሜይል፦ boe@mcpsmd.org መገናኘት ይችላሉ።

### የሞንትጎመሪ ካውንቲ ካውንስል ስብሰባዎች

ስብሰባዎች የሚካሄዱት በሚከተለው አድራሻ ነው፦
Werner County Office Building at 100 Maryland Avenue, Rockville, MD 20850.
መደበኛ ስብሰባዎች እንደሚካሄዱ ለማረጋገጥ በስልክ ቁጥር 240-777-7900 ይደውሉ ወይም በኢ-ሜይል፦ county.council@montgomerycountymd.gov ይጠይቁ።

### የማህበረሰብ አስፈጻሚ ቦርድ ስብሰባዎች

በየወሩ አራተኛው ማክሰኞ ምሽት በዙም ወይም በዚህ አድራሻ ይካሄዳል፦
1401 Rockville Pike, Rockville፣ MD

### የፖሊሲ ካውንስል ስብሰባዎች

በየወሩ ስለሚካሄዱት የፖሊሲ ካውንስል ስብሰባዎች ቀን፣ ሠዓት፣ እና ቦታ በዚህ መጽሔት ላይ ይመልከቱ።

# የቅድመ ሙዓለ ህፃናት እና ሄድ ስታርት ፕሮግራም አገልግሎት አይነቶች

## የፕሮግራም ንድፍ እና አስተዳደር

### አስተዳደር

የአስተዳደር አገልግሎት መስክ አጠቃላይ የፕሮግራም ቅንብር፣ የበጀት ዝግጅት፣ እና በት/ቤት ስርአትና በማህበረሰብ ውስጥ ግንኙነቶችን ያመቻቻል፤ Mrs. Jessica Blasic, ሱፐርቫይዘር

### የፖሊሲ ካውንስል

ስለ ፕሮግራሙ ውሳኔዎችን ለመስጠት ቅድመ ሙዓለህፃናት/ሄድ ስታርት ፕሮግራም ከእያንዳንዱ ቅድመ ሙዓለህጻናት/ሄድ ስታርት ት/ቤት ከወላጆች/ሞግዚቶች የተመረጡ የፖሊሲ አውጪ ካውንስል (PC) አለ። የቀድሞ ወላጆች/ሞግዚቶች እና ሌሎች የማህበረሰብ ተወካዮችም እንደዚሁ በፖሊሲ ካውንስል ያገለግላሉ። ካውንስሉ በየወሩ ሶስተኛ ሐሙስ 6፡00 ሰዓት p.m. ላይ በዙም (Zoom) ስብሰባ ያደርጋል።

በኦክቶበር ወር፣ የፖሊሲ ካውንስሉ ተወካዮች የመጪውን አመት ረቂቅ የበጀት ፕሮግራም ይቀርብላቸውና የወላጅ ትግበራ/Parent Activity ፈንድ እንዴት እንደሚወጣ ይወስናሉ። ሁሉም ወላጆች/ሞግዚቶች የፖሊሲ ካውንስል ድምፅ ይሰጣሉ ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ሁሉም ወላጆች/ሞግዚቶች በሁሉም ስብሰባዎች ለመሣተፍ ይችላሉ። የእርስዎ አስተዋፅኦ ይፈለጋል። የፖሊሲ ካውንስል አባላት አዲስ ምርጫ በዲሴምበሩ ስብሰባ ይከናወናል። ት/ቤትዎ መወከሉን እርግጠኛ ይሁኑ። ጃኑወሪ ለትምህርት ስርአቱ የበጀት ወር ነው። ስለ ሙዓለህፃናት/ሄድ ስታርት ትምህርት ባጀት በተመለከተ የፖሊሲ ካውንስል ተወካይ በትምህርት ቦርድ ፊት በመቅረብ መቼ ምስክርነት እንደሚሰጥ የሚተላለፈውን ማስታወቂያ ይመልከቱ። በስብስባው በመገኘት ድጋፍዎን ያሳዩ። ስለ ቅድመ-ሙዓለህፃናት/ሄድ ስታርት መልካም ነገር በመናገር/በማወጅ ይርዱ። የምልመላ ኮሚቴ ብቃት ያላቸው ቤተሰቦች ጋር እንዴት እንደሚደርስ እቅድ ያዘጋጃል፣ መመርያዎችን ይሰጣል፣ የመጪውን አመት የልጆች ምልመላም ያቅዳል። ለበለጠ መረጃ ለወላጅ ተሳትፎ/የበጎ ፈቃድ ስፔሻሊስት ሚ/ር ሮቤርቶ ፍሎሬስ 240-740-4530 ይደውሉ።

# የወላጅ፣ የቤተሰብና የማህበረሰብ ተሳትፎ

### ማህበራዊ አገልግሎቶች

ይህ የአገልግሎት መስክ ቤተሰቦችን መልምሎ ይመዘግባል ቤተሰቦችን ከማህበራዊ አገልግሎቶችና መገልገያዎች ጋር ለማገናኘት ያግዛል። ለያንዳንዱ መማርያ ክፍል አንድ የቤተሰብ አገልግሎት ሰራተኛ ይመደባል ለቤተሰቦችም ድጋፍና የመገልገያ እርዳታ ያቀርባል። የልጅዎን የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ ስም እና የስልክ ቁጥር ለማግኘት በዚህ ካላንደር የፊትለፊት ገጽ ላይ ይመልከቱ፦ ሌሎች ጥያቄዎች ካለዎት ሚስ ሊሳ ኮንሎን፣ የማህበራዊ አገልግሎት ስፔሻሊስት (Ms. Lisa Conlon, social services specialist)፣ በስልክ ቁጥር፦ 240-740-4530 ያነጋግሩ።

### የቤተሰብ ተሳትፎ

እያንዳንዱ ክፍል ወላጆች/ሞግዚቶች እርስ በእርስ ለመተዋወቅ የሚያስችላቸው፣ የመማሪያ ክፍሎችንና የሚያስተምሩትን ቡድን ለመጎብኘት፣ ስለ ልጆች እድገት፣ ምንባብ እና ሂሳብ፣ መሠረተ ትምህርት፣ ሥርዓተ ምግብ፣ ደህንነት፣ ጤንነት፣ ስነጥበባት እና እድጥበባት፣ እንዲሁም ፕሮግራሙ እንዴት እየሠራ እንዳለ ለማወቅ የሚያስችሉ የወላጅ/ሞግዚት ስብሰባዎች ይካሄዳሉ። ከልጅዎ ጋር በት/ቤት አውቶቡስ ሊጓዙ ይችላሉ፣ እና ሄድ ስታርት ወላጆች/ሞግዚቶች ምሣ ሊኖር ይችላል። ሁሉም ስብሰባዎች የታቀዱ እና በቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኞች በመታገዝ በወላጆች/ሞግዚቶች የሚካሄዱ ናቸው። የወላጅ/ሞግዚት በጎ ፈቃድ አገልጋዮች ጥያቄዎች ላይ ያተኮረ ስብሰባ ለማዘጋጀት መመዝገብ ይችላሉ። የሄድ ስታርት ታናሽ ወንድም/እህት ማምጣት ይችላሉ። ጥያቄዎች አሉ? ለቤተሰብ አገልግሎት ሰራተኛ 240-740-4530 ይደውሉ።

ወላጆቻቸው/ሞግዚቶች ሲሳተፉ ልጆች የትምህርቱ ተጠቃሚ ይሆናሉ። ቅድመ ሙዓለህፃናት/ሄድ ስታርት ፕሮግራም ወላጆች/ሞግዚቶች ሊሳተፉ የሚችሉባቸው በርካታ መንገዶች አሉ፦ በመማሪያ ክፍል በጎ ፈቃደኛ መሆን፣ ቅድመ ሙዓለህፃናት/ሄድ ስታርት ፕሮግራም እንዴት መካሄድ እንዳለበት ውሳኔ መስጠት፣ እቤት ውስጥ ከልጆች ጋር የማስተማር እንቅስቃሴዎችን የትምህርት ፕሮግራሞችና እንቅስቃሴዎችን እቅድ ማዘጋጀት እና የወላጅ/ሞግዚት ትምህርት ፕሮግራሞችን ለማዳበር ከሠራተኞች ጋር እና ከሌሎች ወላጆች/ሞግዚቶች ጋር በትብብር መሥራት። ወላጆች/ሞግዚቶች በየወሩ ስብሰባ ያደርጋሉ፣ እና እያንዳንዱ ክፍል ለካውንቲ አቀፍ የፖሊሲ ካውንስል ተወካይ ይመርጣል። ለቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛ፣ ለፖሊሲ ካውንስል ሊቀመንበር፣ ወይም ለወላጆች ተሳትፎ/የበጎ ፈቃድ ስፔሻሊስት ሚስተር ሮቤርቶ ፍሎሬስ 240-740-4530 ይደውሉ።

### ሙያ ማዳበር

በቅድመ-ሙዓለህፃናት/ሄድ ስታርት ወላጆች/ሞግዚቶች እንደ ረዳት አስተማሪ ወይም በተተኪነት የመቀጠር እድሎች አሉ። ትምህርትዎን ለማጠናቀቅ ወይም ሌላ ማናቸውም የሙያ ግብ ለመድረስ ቅድመ-ሙዓለህፃናት/ሄድ ስታርት ጽ/ቤት በስልክ ቁጥር፦ 240-740-4530 በመደወል ለማሳካት ይችላሉ።

### የማህበረሰብ መገልገያዎች/ሪሶርሶች

"Pre-K/Head Start" ጠቃሚ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን የሚዘረዝር መመሪያ አዘጋጅቷል፣ ይህንኑ ጠቃሚ የማህበረሰብ ሪሶርስ መመሪያ ያሠራጫል። መመሪያው የሚያካትተው የምግብ እርዳታ፣ የጤና ክሊኒኮችን፣ የመኖሪያ/መጠለያ ቤት፣ እና አገልግሎት ላይ የዋሉ አልባሳት የሚገኙበት አካባቢ የስልክ ቁጥሮችን ነው። የዝርዝሩን ቅጅ ካልደረሰዎት የሪሶርስ መመሪያ ዝርዝር ለማግኘት የቤተሰብ አገልግሎት ሠራተኛን ይጠይቁ።



| ሴፕተምበር 2023 | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| S/እ | M/ሰ | T/ማ | W/ሮ | T/ሐ | F/ዓ | S/ቅ |
| | | | | | 1 | 2 |
| 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
| 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 |
| 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 |
| 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |

# ኦክቶበር 2023

| ኖቬምበር 2023 | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| S/እ | M/ሰ | T/ማ | W/ሮ | T/ሐ | F/ዓ | S/ቅ |
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
| 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 |
| 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 |
| 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | | |

| እሁድ | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5<br>የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ—6፡00 PM—ቨርቹወል ስብሰባ/ዙም (Zoom) | 6<br>የሄድ ስታርት ለወላጆች የሚሰጡ መግለጫዎች ይጠናቀቃሉ | 7 |
| 8 | 9<br>ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት አይኖርም። | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| 15 | 16 | 17 | 18<br>ለቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሔድ ስታርት አስተማሪዎች ስልጠና— ለቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሔድ ስታርት ተማሪዎች ትምህርት አይኖርም(ቡድን A) | 19<br>የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ— 6፡00 PM—ቨርቹወል ስብሰባ/ቨርቹወል (Zoom) | 20 | 21 |
| 22 | 23 | 24 | 25<br>ለቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሔድ ስታርት አስተማሪዎች ስልጠና— ለቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሔድ ስታርት ተማሪዎች ትምህርት አይኖርም(ቡድን B) | 26 | 27 | 28 |
| 29 | 30 | 31<br>የቅድመ ሙዓለህፃናት መግለጫ ይጠናቀቃል | | | | |

ከተለያዩ ዛፎች ቅጠሎች መሰብሰብ፣ ተመሳሳዮቹን መለየት፣ እና በእግር መንገድ ጠመኔ ዙርያቸውን መሳል።

# አስፈላጊ መረጃዎች

### ቀዳሚ ሄድ ስታርት/Early Head Start

ቀዳሚ ሄድ ስታርት/Early Head Start እድሜአቸው ከወሊድ እስከ 3 አመት የሆኑ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች አስደናቂ ፕሮግራም ነው። ፕሮግራሙ ከሄድ ስታርት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ በርካታ አገልግሎቶች እና የተወሰኑ ልዩ የሆኑትን ለቀዳሚ ሄድ ስታርት ያቀርባል። ለማመልከት፣ ቤተሰቦች እርጉዝ ወይም እድሜአቸው 26 ወር ወይም ከዚያ በታች የሆኑ ልጆች ያሏቸው መሆን አለባቸው። ስለ ፕሮግራሙ ተጨማሪ መረጃ የሚያገኙበትን እነሆ፡- በጌትስበርግ እና በአፕካዉንቲ (Gaithersburg and Upcounty) አካባቢዎች፡- ለቤተሰብ አገልግሎቶች Inc፣ ቅድመ ሄድ ስታርት 301-840-3272 ይደዉሉ። በሲልቨር ስፕሪንግ እና ሮክቪል አካባቢዎች (Silver Spring and Rockville areas) ፡- The Reginald S. Lourie Center, Early Head Start በስልክ ቁጥር 301-891-1900 ይደዉሉ። በላንግሊ ፓርክ/ሲልቨር ስፕሪንግ (Langley Park/Silver Spring) አካባቢ፡- CentroNía, Early Head Start በስልክ ቁጥር 301-543-8040 ይደዉሉ።

### የህፃናት እንክብካቤ

የልጅ ተንከባካቢ የሚፈልጉ ወላጆች/አሳዳጊዎች ወደ LOCATE መደወል ይችላሉ፡- የሕፃናት እንክብካቤ በስልክ ቁጥር 1-877-261-0060 ወይም ቻይልድሊንክ (ChildLink) 240-777-3997 በነፃ ለመርዳት ፈቃድ ያለው የሕጻናት ተንከባካቢ፣ የትምህርት እድሜ ፕሮግራም፣ የሰመር ካምፕ፣ ቅድመ ትምህርት፣ እና/ወይም የመሰናዶ ት/ቤት ፕሮግራም ለማግኘት። ጠቋሚ/LOCATE፣ የእንክብካቤ ሰዓቶችን፣ ቦታ፣ የልጆች ብዛትና እድሜ፣ እና የልጅ እንክብካቤ ክፍያ በመሳሰሉ፣ በእያንዳንዱ ቤተሰብ ፍላጎቶች ላይ በመመስረት አገልግሎት ሰጪዎችን ለይቶ ይገልጻል። ይህን አገልግሎት በበርካታ ቋንቋዎች ማግኘት ይቻላል። ጠቋሚ/LOCATE በትምህርት ቤቱ የአገልግሎት ክልል ውስጥ ወይም አጠገብ የሚገኙትን አቅራቢዎች ለይቶ ማወቅ ይችላል። በተጨማሪ፣ ካውንስለሮች መልካም ፕሮግራሞችን ስለ መለየት ጥቆማዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ትክክለኛ ፕሮግራም ለልጃቸው እንዲመርጡ ለማገዝ ለክትትል ቀላል የሆኑ ጥቆማዎችን ይሰጣሉ።

ጠቋሚ/LOCATE፡- "Child Care" በሜሪላንድ የትምህርት ዲፓርትመንት የቤተሰብ የልጅ እንክብካቤ ሰጪዎችንና የልጆች እንክብካቤ ማእከሎችን (የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት የልጆች እንክብካቤ ጽ/ቤት) ተቀባይነት ያላቸውን ሁለቱንም ለይቶ ያሣያል። ወላጆች/አሳዳጊዎች የሚከተሉትን ባህርዮች የሚያንፀባርቁ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን ፕሮግራሞች ማግኘት አለባቸው፡- ሰራተኛው/ዋ የልጆቹን እድገታዊ ፍላጎቶች የሚገነዘብ-የምትገነዘብ፤ ፕሮግራሙ የተለያዩ ትምህርታዊ ቁሳቁሶች ያሉት፣ አቅርቦቶች፣ እና ከተገልጋዮች እድሜ ጋር አግባብ የሆኑ መጫወቻዎች ያሏቸው፤ ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች መልካም አቀባበል ያላቸውና የሚያሳትፉ፤ መርሃግብሮችን፣ ፖሊሲዎችን፣ እና ፕሮግራሞችን በሚመለከት ሰራተኛው(ዋ) ከት/ቤት ባልደረቦች ጋር በትብብር አብረው የሚሠሩ። በስቴት እና የካውንቲ ህጎች ድንጋጌ መሠረት ከ8 አመት በታች የሆኑ ልጆች ሁልጊዜ በወላጅ/አሳዳጊ፣ የልጅ ተንከባካቢ፣ ወይም ቢያንስ 13 አመት እድሜ ባለው/ባላት ልጅ ቁጥጥር እንዲጠበቁ ይደነግጋሉ። ወላጆች/አሳዳጊዎች ስለ ልጅ እንክብካቤ መረጃዎች መስመር ላይ www.marylandfamilynetwork.org መፈለግ ይችላሉ።

በሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና ጥበቃ እና ሰብአዊ አገልግሎት በኩል ለህጻን እንክብካቤ ለመክፈል የገንዘብ እርዳታ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ፡- የሠራተኛ ቤተሰብ ድጋፍ (WPA) 240-777-1177 ይደዉሉ። ቅጂው እርስዎ ብቁ መሆንዎን ለመወሰን እንዴት እንደሚቻል ጨምሮ አጠቃላይ መረጃ ይሰጣል። የሜሪላንድ የሕፃናት እንክብካቤ ስኮላርሺፕ ፕሮግራም (The Maryland Child Care Scholarship Program) ብቁ ለሆኑ ሠራተኛ ቤተሰቦች ለሕፃናት እንክብካቤ ወጪ እገዛ ይሰጣል። 1-877-227-0125 ይደውሉ።



## የህጻናት እድገት እና የጤና አገልግሎቶች

### የአካል ጉዳተኛ/ስንክልና ያላቸዉ ልጆች

ሄድስታርት በፌደራል በጀት የሚካሄድ ፕሮግራም ነዉ። የአካል ጉዳተኛ/ስንክልና ያላቸዉ ልጆች ለፕሮግራሙ ከሚመዘገቡት ከመቶ እጅ አስሩን (10 ፐርሰንት) እንዲይዙ ያዛል። አካል ጉዳተኛ/ስንክልና ያላቸዉ ልጆች የቅድመ-መዋዕለ ህጻናት/ሄድስታርት መማሪያ ክፍሎችን ስንክልና ከሌላቸው ጋር ይጋራሉ (አካታች ሞዴል) እናም የቅድመ-መዋዕለ ህጻናት/ሄድስታርት ልጆች የሚያገኟቸዉን ሁሉንም አገልግሎቶችና መብቶች ያገኛሉ። የመማሪያ ክፍል እንቅስቃሴዎች እና ተሞክሮች አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜና ቦታ ሁሉ የአካል ጉዳተኛ ልጆችን በሚያሳትፍ መልኩ እንዲስተካከሉ ይደረጋል።

ሁሉም ልጆች አንድ ላይ የሚማሩበት እና የሚያድጉበት ጊዜ እንደመሆኑ መጠን፣ ወላጆች/ሞግዚቶች፣ አስተማሪዎች፣ እና ልጆች በአካታች ሞዴል ይደሰታሉ። ስለ ልጃቸው እድገት ከወላጆች/አሳዳጊዎች ለሚነሱ ጥያቄዎች የሥራ ባልደረቦች መልስ ይሰጣሉ። በተጨማሪም፣ የሥራ ባልደረቦች ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች ልጃቸዉ እርዳታ በሚያስፈልጋቸው በተለየ አካባቢ የሚያግዝ/የሚረዳ በቤት ውስጥ የሚከናወኑ ተግባሮችን ይሰጣሉ። ልጆች በተለያዩ የእድገት ዘርፎች የማጣሪያ ምርመራ ይደረግላቸዋል (ትምህርታዊ፣ የንግግር/የቋንቋ፣ ዕይታ፣ ጥርስ እና መስማት።) በማጣሪያ ምርመራው መሰረት፣ የትምህርት ስንክልና ከተጠረጠረ፣ የግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን(ለምሳሌ፣ መምህራን፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና የት/ቤት ስነ-ልቦና ባለሙያ፣ ልዩ ትምህርት አስተማሪ፣ የስነ-ልሣን ንግግር ባለሙያ (ፓቶሎጂስት)፣ ነርስ፣ ወዘተ) ተጨማሪ ምዘናዎች/ምርመራዎች እንደሚያስፈልጉ ለመወሰን ይሰበሰባሉ። ሌሎች ተጨማሪ ምዘናዎች/ምርመራዎች እንዲደረጉ ከተመከረ/ከተወሰነ፣ ትምህርት ቤቱ ለምርመራዎቹ የወላጅ/የአሳዳጊ ስምምነት ማግኘት አለበት።

ምርመራዎቹ እና ግምገማዎቹ ከተጠናቀቁ በኋላ፣ IEP ቡድን ምን አይነት የትምህርት ስንክልና እንደሆነ መወሰን አለበት፣ ከሆነም የትኛው የፌዴራል የትምህርት ስንክልና ኮዶች የተማሪዉን/ዋን ስንክልና እንደሚገልፅ ይለያል። የትምህርት ስንክልና መኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ፣ እና IEP ቡድን ስንክልናዉ በተማሪው/ዋ መማር ላይ ተፅእኖ ማሳደሩን ከወሰነ፣ ተገቢ ግቦች እና የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ላይ ዉይይት ይደረጋል ።

ተፈላጊ አገልግሎቶች በቅድመ-መዋዕል ህጻናት/ሄድ ስታርት ፕሮግራም ወይም በሌላ MCPS ፕሮግራሞች በኩል ሊሰጡ ይችላሉ። ልጅዎ በቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድ ስታርት የመማሪያ ክፍል ሊቀርብ ከሚችል የበለጠ የልዩ ትምህርት አገልግሎት ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከሚቀርቡ አገልግሎቶች የተለየ የሚያስፈልግ ከሆነ፣ የቅድመ መዋዕለ ሕጻናት/ሄድ ስታርት ሰራተኛ የተወሰነዉን/የተፈለገውን አገልግሎት ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዴት/ከየት እንደሚያገኙ ሊረዷቸው ይችላሉ።

በልጅዎ እድገት ውስጥ ሊያዩዋቸው የሚገቡ ነገሮች፡-

- ንግግርና ቋንቋ፡- ልጅዎ በግልጽ መናገር እና ቋንቋን መረዳት ይችላል/ትችላለች?
- መረዳት እውቀት ወይም ግንዛቤ/Cognitive፡- ልጅዎ ተመሳሳይ ዕድሜ ካላቸው ከሌሎች ልጆች ጋር እኩል በሆነ መልኩ እየተማረ እና እያደገ ነው ወይ?
- ግርድፍና ረቂቅ እንቅስቃሴ/Gross and Fine Motor፡- ልጅዎ "ገልጃጃ" ነው/ናት ወይም ልጅዎ በእጁ/ጇ በመጠቀም በብሎክ ለመጫወት ወይም በወረቀት ላይ ለመጫር ችግር አለበት/ባት ወይ?
- ማህበራዊ/ስሜታዊ ልጅዎ ከሌሎች ልጆችና ጎልማሶች ጋር ይስማማልን/ትስማማለችን?
- ማሳሰብያ፡- ልጅዎ በዕድሜ እኩያ ከሆኑ ከሌሎች ልጆች ይልቅ በእርጋታ ቁጭ የማለት ወይም ትኩረት የመስጠት ችግር አለበት/ባት ወይ?
- ማዳመጥ/መስማት ወይም ማየት፡- ልጅዎ መጽሐፍትን ወይም ቴሌቪዥንን ሲመለከት/ስትመለከት ዓይኑን/ኗን በከፊል ይጨፍናል/ትጨፍናለች ወይ? ልጅዎ በአካባቢው/ዋ ለሚፈጠር ድምጽ በአግባቡ ምላሽ ይሰጣል/ትሰጣለች ወይ ?

የልጅዎን እድገት በተመለከተ ስጋት ካለዎት፣ ለአስተማሪዎ ያሳውቁ፣ ወይም ለቅድመ-መዋዕለ ህፃናት/ሄድስታርት ክፍል በ240-740-4530ይደውሉ።



# ኖቬምበር 2023

| ኦክቶበር 2023 | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| S/እ | M/ሰ | T/ማ | W/ሮ | T/ሐ | F/ዓ | S/ቅ |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 |
| 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 |
| 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 | 21 |
| 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 | 28 |
| 29 | 30 | 31 | | | | |

| ዲሴምበር 2023 | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| S/እ | M/ሰ | T/ማ | W/ሮ | T/ሐ | F/ዓ | S/ቅ |
| | | | | | 1 | 2 |
| 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 |
| 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 |
| 17 | 18 | 19 | 20 | 21 | 22 | 23 |
| 24 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |
| 31 | | | | | | |

| እሁድ | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርት አይኖርም፥ የሩብ አመት እቅድ መጨረሻ | 2 የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ—6:00 P.M.—ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) | 3 | 4 |
| 5 | 6 | 7 | 8 | 9 የአባትነት ተግባር—6:30 P.M.—ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) | 10 | 11 |
| 12 | 13 | 14 | 15 | 16 የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ—6:00 P.M.—ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) | 17 | 18 |
| 19 | 20 የወላጅ-መምህር ኮንፈረንስ—ለቅድመ መዋዕለ ህጻናት እና ለሄድ ስታርት ተማሪዎች ትምህርት ቤት የለም። | 21 የወላጅ-መምህር ኮንፈረንስ—ለቅድመ መዋዕለ ህጻናት እና ለሄድ ስታርት ተማሪዎች ትምህርት ቤት የለም። | 22 ታንክስጊቪንግ/THANKSGIVING—ት/ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ናቸው | 23 ታንክስጊቪንግ/THANKSGIVING—ት/ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ናቸው | 24 ታንክስጊቪንግ/THANKSGIVING—ት/ቤቶች እና ቢሮዎች ዝግ ናቸው | 25 |
| 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | | |

**የጥንብ አንሺ አደን መሄድና ሁሉን ነገሮች በABC ስርአት ማሰለፍ።**

## ትምህርት

ፕሮግራሞች የተነደፉት/የተዘጋጁት የእያንዳንዱን ልጅ ፍላጎት ለመድረስ እና ልጆቻቸውን በቤታቸው ለመርዳት/ለማገዝ ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር ሃሳቦችን ለመለዋወጥ ነው። ማእከሎቻችን ልጆችን የመማርያ አካባቢዎች እና በማህበራዊ፣ በአእምሮአዊ፣ በአካላዊ፣ እና በስሜታዊ እድገት የሚደግፏቸው የተለያዩ ተሞክሮዎችን ያቀርባሉ። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ቅድመ-መዋእለ ህጻናት/ሄድስታርት ከእርስዎ እና ከልጅዎ ጋር አብረው የሚሰሩ የንግግር ፓቶሎጂስቶች እና ሳይኮሎጂስቶች አሉት። የትምህርት አገልግሎት ስፔሻሊስት በስልክ ቁጥር 240-740-4530 ሊገኝ ይችላል። ወላጆች/አሳዳጊዎች እንዲጎበኟቸው፣ በጎ ፈቃደኞች እንዲሆኑ፣ የመስክ ጉዞ እንዲያደርጉ፣ ፓርቲ ሲኖር እንዲረዱ እና/ወይም በቤት ውስጥ እንዲረዱ ተጋብዘዋል። የበጎ ፈቃድ አግልግሎት ለመስጠት ለበለጠ መረጃ ቅድመ-መዋእለ ህጻናት/ሄድስታርት ቢሮ ለሚስተር ሮቤርቶ ፍሎሬስ 240-740-4530 ይደውሉ።

## አስቸኳይ ሁኔታዎች

እስፈላጊ/ጠቃሚ ነው! ት/ቤቱ እና የቅድመ-ሙዓለህፃናት/ሄድ ስታርት ጽ/ቤት የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ በሚደረግበት ወቅት እርስዎ ካልተገኙ ሌላ ሰው ለማግኘት የሚቻልበትን ስልክ ቁጥሮች መስጠትዎን እባክዎን ያረጋግጡ። የስልክ ቁጥርዎን ወይም አድራሻዎን ከቀየሩ፣ ለት/ቤቱ እና የቅድመ-ሙዓለህፃናት/ሄድ ስታርት ጽ/ቤት የስልክ ቁጥር 240-740-4530 በመደወል የእርስዎን አዲሱን የስልክ ቁጥር እና አድራሻ ያሳውቁ።

## ጤና

ልጆች እንደ የደም ምርመራዎች፣ የማየትና የመስማት ችሎታዎች እና የጥርስ ህክምና ምርመራ ይደረግላቸዋል። ካስፈለገ እርስዎ ምንም ወጪ ሳይከፍሉ የጥርስ አገልግሎት የጥርስ ንፅህና፣ የጥርስ ህክምና ይደረጋል። የጤና አገልግሎቶች ማናጀር ሚ/ር ቤካ ኡርጌሳ (Mr. Beka Urgessa) ናቸው። የስልክ ቁጥር፡- 240-777-1553

## የጤና ክሊኒኮች

መረጃ ለማግኘት፣ ለእርዳታ እና ለጤና ጥበቃ መገልገያዎች፣ ወደ ጤና እንክብካቤ ብቁነት ክፍል (OESS) ይደውሉ፡ ሮክ ቪል ጤና ጣቢያ/Rockville Health Center, 240-777-3120፣ ሲልቨር ስፕሪንግ ጤና ጣቢያ/Silver Spring Health Center, 240-777-3066፣ እና ጀርመንታዎን ጤና ጣቢያ/Germantown Health Center, 240-777-3591

## ለህመምተኞች እንክብካቤ

21 አመት እድሜ በታች ለሆኑ ልጆችና ወጣቶች ህክምና ኮሙኒቲ ክሊኒክ Community Clinic for sick care 8630 Fenton Street, Suite 1200, Silver Spring, 301-585-1250፣ 7676 New Hampshire Avenue, Takoma Park, 301-431-2972; ወይም 200 Girard Street, Suite 212, Gaithersburg, 301-216-0880። ደውለው ቀጥሮ መያዝና የገቢ መረጃ ይዘው መምጣት አለብዎት።

## የፈቃድ ወረቀት

ለልጅዎ በቅድመ-ሙዓለህፃናት/ሄድ ስታርት ፕሮግራም የጤና ምርመራ እና የጥርስ አገልግሎት ካስፈለገ የፈቃድ ወረቀቱን ፈርመው መመለስ አለብዎት።

## አመጋገብ

ቅድመ-ሙዓለህፃናት/ሄድ ስታርት ፕሮግራም፣ ፐብሊክ ስኩልስ የሚቀርብ አይነት ተመሣሣይ የምግ ፕሮግራም ነው ያለው። ለወላጆች/ሞግዚቶች እና ልጆች ስለ ስነ-አመጋገብ ትምህርት የተዘጋጁ የትምህርት እድሎች ይገኛሉ። ወደ ቅድመ-ሙዓለህፃናት/ሄድ ስታርት ፕሮግራም ጽ/ቤት በስልክ ቁጥር፡- 240-740-4530 በመደወል ስለ ስነ-አመጋገብ መረጃ ያገኛሉ።

## የፕሮግራሙ የውስጥ-ግምገማ

የወላጆች እና የሠራተኞች ኮሚቴ ስለ ቀዳሚ ጀማሪ/ሄድ ስታርት ፕሮግራም ዓመታዊ ግምገማ መሙላት አለባቸው። መረጃ ለማግኘት ወይም ኮሚቴውን ለመቀላቀል ለሚስተር ሮቤርቶ ፍሎረስ 240-740-4530 ይደውሉ።

## የጤና አገልግሎቶች

ለቅድመ-መዋለ ሕጻናት/ሄድ ስታርት እንደ ቅድመ ሁኔታ፣ ሁሉም ተማሪዎች አካላዊ ምርመራ፣ የስቴትና የፌድራል ተፈላጊ ክትባቶች፣ የደም ምርመራና የጥርስ ምርመራ ማድረግ አለባቸው። ልጅዎ አካላዊ ምርመራ እና ክትባቶች ለመቀበል የጤና እንክብካቤ ምንጭ ከሌለው/ከሌላት፣ እነዚህን አገልግሎት ማግኘት እንዲ(ድት)ችል እባክዎን የልጅዎ አስተማሪ፣ የቤተሰብ አገልግሎት ሰራተኛ፣ ወይም የት/ቤቱ ነርስ እንዲያውቁ ያድርጉ። ለስቴት እና ለአካባቢ የጤና እና የአመጋገብ ፕሮግራሞች፣ በሚከተሉት ቦታዎች በሚገኙ የብቁነት እና የድጋፍ አገልግሎቶች ጽ/ቤት (OESS) ለቤተሰብዎ ፋይናንሳዊ ድጋፍ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡-

12900 Middlebrook Road, Germantown, MD 20874 240-777-3591
1401 Rockville Pike, Rockville, MD 20852 .240-777-3120
8630 Fenton Street, Silver Spring, MD 20910240-777-3066
4910 Macon Road, Rockville, MD 20852 . .240-740-4430

በሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና ጥበቃ ማዕከሎች እና MCPS Health Services Center at Rocking Horse Road Center (4910 Macon Road, Rockville) በሚገኝ የ MCPS የጤና ጥበቃ አገልግሎት ማእከል ሁሉም ክትባቶች ለቤተሰቦች በአነስተኛ ወጪ ይሰጣሉ። እባክዎን ልጅዎ የወሰዳቸውን ክትባቶች ማስረጃ በሚገባ ይያዙ።

በትምህርት አመት ውስጥ ልጅዎ የጥርስ፣ የመስማት፣ የማየት፣ የቁመት እና የክብደት ምርመራዎች/መለኪያዎች ይደረግለ(ላ)ታል።

## ህክምናዎች

ልጅዎ ማንኛውም መድሃኒት (የታዘዘለ(ላ)ት ወይም ያለ ማዘዣ) በትምህርት ቀን መውሰድ የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት ከሆነ፣ ፈቃድ ባለው ሐኪም የተሰጠ የመድኃኒት ትዕዛዝ እና MCPS ቅጽ 525-13 ለትምህርት ቤቱ የታዘዘ መድሃኒትን የማስተዳደር ፍቃድ ሞልተው ማቅረብ አለብዎት (ቅጹ በልጅዎ ትምህርት ቤት እና MCPS ድረ ገጽ ላይ ይገኛል። www.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/pdf/525-13.pdf በሐኪም የታዘዘ መድሃኒት በመድሃኒት ባለሙያ በተገቢዉ ምልክት ተደርጎበት በትክክለኛ የመያዣ እቃ ወደ ትምህርት ቤት መምጣት አለበት። ያለሃኪም ትእዛዝ የሚወሰድ ከመድሃኒት መሸጫ ቤት መደርደሪያ ላይ የሚገዛ መድሃኒት በተመረተበት ኦርጅናል እቃ ላይ በትክክል የተከደነ እና የታሸገ መሆን አለበት። MCPS ቅጽ 525-14፣ አናፍለክሲስ (Anaphylaxis) ያለበት-ያለባት ተማሪ ድንገተኛ እርዳታ ፣ epinephrine auto-injectors ለመጠቀም ህጋዊ ፈቃድ ባለው/ባላት የህክምና ባለሙያ ተመራጭ የማዘዣ ቅጽ (www.montgomeryschoolsmd.org/departments/forms/pdf/525-14.pdf)። ሁሉም ዓይነት መድኃኒት በወላጅ/በሞግዚት አማካይነት ለት/ቤት በእጅ መሰጠት አለበት። ልጅዎ የጤና ችግር፣ በተለይ አስቸኳይ እርምጃ የሚጠይቁ እንደ አስም፣ የስኳር በሽታ፣ የሚጥል በሽታ፣ ወይም የተባይ ንድፊያ ወይም የምግብ አለርጂ ካለው/ካላት እባክዎን ለርእሰመምህር እና ለት/ቤቱ ነርስ ያስታውቁ።





| ኖቬምበር 2023 | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| S/እ | M/ሰ | T/ማ | W/ሮ | T/ሐ | F/ዓ | S/ቅ |
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 |
| 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 |
| 19 | 20 | 21 | 22 | 23 | 24 | 25 |
| 26 | 27 | 28 | 29 | 30 | | |

# ዲሴምበር 2023

| ጃኑዋሪ 2024 | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| S/እ | M/ሰ | T/ማ | W/ሮ | T/ሐ | F/ዓ | S/ቅ |
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
| 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 |
| 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 21 | 22 | 23 | 24 | 25 | 26 | 27 |
| 28 | 29 | 30 | 31 | | | |

| እሁድ | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 1 | 2 |
| 3 | 4<br>ብሔራዊ የሄድ ስታርት የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ኮንፈረንስ፣ New Orleans, LA | 5<br>ብሔራዊ የሄድ ስታርት የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ኮንፈረንስ፣ New Orleans, LA | 6<br>ብሔራዊ የሄድ ስታርት የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ኮንፈረንስ፣ New Orleans, LA<br>ለቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሔድ ስታርት አስተማሪዎች ስልጠና— ለቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሔድ ስታርት ተማሪዎች ትምህርት አይኖርም(ቡድን A) | 7<br>ብሔራዊ የሄድ ስታርት የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ኮንፈረንስ፣ New Orleans, LA<br>የፖሊሲ ካውንስል ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ስብሰባ—6:00 P.M.—ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) | 8 | 9 |
| 10 | 11 | 12 | 13<br>ለቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሔድ ስታርት አስተማሪዎች ስልጠና— ለቅድመ-መዋእለ ህጻናት እና ሔድ ስታርት ተማሪዎች ትምህርት አይኖርም(ቡድን B) | 14 | 15<br>ዊንተር ላይትስ (ብርሃን) ክውነት | 16 |
| 17 | 18 | 19 | 20 | 21<br>የፖሊሲ ካውንስል ወርሃዊ ስብሰባ—6:00 P.M.—ቨርቹዋል ስብሰባ/ዙም (Zoom) | 22 | 23 |
| 24<br>31 | 25 | 26 | 27 | 28 | 29 | 30 |

**የክረምት (ዊንተር) እረፍት**

ለተማሪዎች እና ለአስተማሪዎች ት/ቤት አይኖርም፣ ቢሮዎች ዝግ ናቸው ዲሴምበር 25 እና ጃኑዋሪ 1

**ከጓደኛ ጋር ሆኖ ኩኪዎች/ብስኩቶች ማብሰል፣ ለክቶ መቁጠር፣ ስለተሞክሮው መወያየት።**

## ህመም/በሽታ

ልጅዎ ትኩሳት ካለበት/ካለባት፣ መጥፎ ሳል፣ ወይም ጤንነት ካልተሰማው/ካልተሰማት፣ እባክዎ እቤት ያቆዩዋቸው። ልጅዎ ህመም እየተሰማው/ት በት/ቤት ደስተኛ አይሆንም/አትሆንም። ልጅዎ (ኩፍኝ፣ ጉድፍ፣ ወ.ዘ.ተ) ከታመመ/ች ዶ/ር ወደ ት/ቤት መመለስ ይችላል/ትችላለች በማለት እስከሚፈቅድ ድረስ እቤት ማቆየት አለብዎት።

## መጓጓዣ/ትራንስፖርት

ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጆቻቸውን ወደ አውቶቡስ ማቆሚያ ለማድረስ፣ በአውቶቡስ ማቆሚያ ቦታ፣ እና ከአውቶቡስ ጣቢያ/ማቆሚያ ወደ ቤት ሲሄዱ ለልጆቻቸው ሃላፊነት አለባቸው። እባክዎ ጠዋት ጠዋት ልጅዎን ወደ አውቶቡስ ያድርሱ በየቀኑ ከሰአት በኋላ ልጅዎን ከአውቶቡስ ይቀበሉ። የአውቶቡስ መርሃግብሮች ግምታዊ ናቸው እናም በአየር ሁኔታ፣ በትራፊክ መጨናነቅ፣ እና በተማሪ ለውጦች ምክንያት ሊለያዩ ይችላሉ። ከመደበኛ መድረሻ ሰዓት ቢያንስ ከአምስት ደቂቃ በፊት በአውቶቡስ ማቆሚያ ላይ መገኘት በጣም ጥሩ ነው። አውቶቡሱን ማግኘት የማይችሉ ከሆነና ሌላ ሃላፊነት የሚሰማው አዋቂ እንዲተካዎ ከመረጡ (ለምሳሌ፣ የልጅ ተንከባካቢ፣ አያት) እባክዎ ለልጅዎ መምህር ወይም ለረዳት አስተማሪ በፅሁፍ ያስታውቁ። ለአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ የትምህርት ቤት ስልክ ቁጥር በሞባይል ስልክዎ ወይም በሌላ ምቹ ቦታ ያስቀምጡ/ይያዙ።

እርስዎ ወይም የእርሶ ተወካይ በተመደበው ሠዓት ልጅዎን ለመረከብ ካልተገኙ፣ ልጅዎ ወደ ትምህርት ቤት ይመለሳል/ትመለሳለች። እርስዎ ወይም ልጅዎን ለመረከብ የወከሉት ሰው ከአውቶቡሱ ልጅዎን ለመቀበል ሶስት ጊዜ ካልቻላችሁ፣ የቤተሰብ አገልግሎት ሰራተኛ ጋር መገናኘት አለብዎት። ችግሮቹ ከቀጠሉ፣ የመጓጓዣ መብቶች ሊቋረጡ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ የአውቶቡስ ላይ የባህሪ ችግሮች የአውቶቡስ መብቶችን ሊያቋርጡ ይችላሉ።

## ልብስ/አልባሳት

